# Global Coalition for Lake Tana Restoration

Address: 4600 14th St. NW, Washington DC 20011
United States
Tel: +1 949 299 8473
Email: management@tanacoalition.org
Website: www.tanacoalition.org

---

ኤፕሪል 21፤ 2018

## Press release

ዓለማቀፉ ጣናን መልሶ ማቋቋም ማህበር ከዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው "ጤና ለጣና" በሚል በቅርቡ ባዘጋጀው ፕሮግራም ባሰባሰበው ገንዘብ ዘመናዊ የእንቦጭ ማጨጃ ማሽን ከኮንቬየር ጋር መግዛቱን አስታወቀ ::

የማህበሩ አስተባባሪ ዶ/ር ሰለሞን ክብረት እንደገለፁት “አሁን የተገዛው ማሽን ከዚህ በፊት ከተገዙት ማሽኖች በአይነቱ የተሻለ ሲሆን እንቦጩን ከማሽን ተቀብሎ ወደ ሃይቁ ዳርቻ ላይ የሚያስተላልፍ ተጨማሪ መሳሪያም አብሮ የተገዛ ሲሆን ይህም የተሰበሰበውም እንቦጭ በአግባቡ ለማጽዳት ይረዳል”::

ማሽኑ ($60,610) ከኮንቬዮር ($31,740 - እንቦጩን ከማሽን ተቀብሎ ወደ ሃይቁ ዳርቻ የሚያስተላልፍ መሳርያ) ከነሙሉ መለዋወጫቸው በ 92,350 USD (2.5 ሚሊዮን ብር) ከካናዳው ማሽን አምራች ድርጅት (Aquamarine) ግዥ መፈጸሙን አስተባባሪው ገልጸዋል።

አስተባባሪው ለዚህ አስተዋፅዖ ላደረጉትና በ"ጤና ለጣና 2018 ዋሺንግተን ዲሲ" ለተሳተፉ ሁሉ ምስጋና አቅርበዋል::

ማህበሩ ከዚህ በፊት አትላንታና እስራኤል ባሰባሰበው ገንዘብ የተገዛውና በመርከብ የተላከው ማሽን በጥቂት ቀናት ውስጥ ጂቡቲ ወደብ እንደሚደርስ አስታውቋል።

በቅርቡ ችካጎ፤ ዳላስና ለንደን እንዲሁም አውስትራሊያ የተለያዬ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች እንደሚካሄዱ ዶ/ር ሰለሞን ገልፀው የጣና ችግር እስኪፈታ ድጋፉ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በውጭ የሚኖሩ በዘርፉ ልምድ ያካበቱ ባለሞያወችን ያቀፈው ይህ ማህበር፤ ከማሽን ግዥ ጎንለጎን ለክልሉ አካባቢ ጥበቃ ቢሮ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት፤ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን በመዘርጋት፤ የተለያዩ ጥናቶች ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በማካሄድ ተጨማሪ አረም ማጨጃ ማሽን ለመግዛትና ጣናን ከአረሙ ለማላቀቅና መልሶ ለማቋቋም ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስተባባሪው ገልጽዋል::

ከሰላምታ ጋር

አቶ መልካምሰው ከበደ
የማህበሩ የህዝብ ግንኙነት ኦፊሰር